**በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሀይማኖት የደብረ ገነት ቅዱስ አማኑኤል ቤተክርስቲያን**

**The Ethiopian Orthodox Tewahdo Religion Debre Genet Kidus Ammanuel Church**



# በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ኃይማኖት የደብረ ገነት ቅዱስ አማኑኤል ቤተክርስቲያን መተዳደሪያ ደንብ

# By-Laws of The Ethiopian Orthodox Tewahdo Religion Debre Genet Kidus Ammanuel Church

## በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሀይማኖት የደብረ ገነት ቅዱስ አማኑኤል ቤተክርስቲያን መተዳደሪያ ደንብ መቅድም

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሃዱ አምላክ አሜን!!!

እኛ በልዩ ልዩ ምክንያት ከሀገራችን ከኢትዮጵያ የወጣን በሰሜ ን አሜ ሪካ፤በፔንስልቫኒያ፤ በፊላደልፊያና አካባቢዋ የምንኖር የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ኃይማኖት ዕምነት ተከታዮች በልዑል እግዚአብሔር ፈቃድ ተሰባስበን በሄድንበት ሁሉ የሚመራንንና የሚጠብቀንን በቦታ የማይወሰን አምላካችንን ስሙ ን ጠርተን እንድናመሰግን በአለንበት አገር መካነ ጸሎት ማዘጋጀት ኃይማኖታዊ ግዴታችን እንደሆነ በመገንዘብ ገንዘባችንን፤ ዕውቀታችንንና ጉልበታችንን አስተባብረን የእግዚአብሔርን ቃል የምንማርበት፤ ስሙ ን ጠርተን የምንጸልይበት በደብረ ገነት ቅዱስ አማኑኤል ስም ሕንጻ ቤተክርስቲያን ገዝተን አገልግሎት ላይ ካዋልን ዓመታት እየተቆጠሩ ነው። ይህ መካነ ጸሎት የዘርና የቋንቋ ልዩነት ሳይኖር የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ኃይማኖት ዕምነትን የሚከተል ሁሉ በእኩልነት የሚጠቀምበት ነው። የእግዚአብሔር ቤት አንድ እምነት ካለው ሁሉ ቤቱ ነውና።

የደብረ ገነት ቅዱስ አማኑኤል ቤተ ክርስቲያን እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ1996 ተመስርቶ በፊላደልፊያና አካባቢው ለሚገኙ ምዕመናን በተዋህዶ እምነትና ሥርዓት መሠረት አገልግሎት ሲሰጥ መቆየቱ ይታወቃል። በዚሁ የጊዜ ሂደት ውስጥ የምዕመናን ቁጥር እየጨመረ በመሄዱ በምዕመናን የጉልበት፤ የገንዘብና የማቴሪያል እርብርብ ከነበርንበት የኪራይ ቦታ ወጥተን የራሳችን የሆነ የቤተክርስቲያን ሕንፃ እ.ኤ.አቆጣጠር በሰኔ 1999 ገዝተን በመስከረም 19 ቀን 1999 ተባርኮ በከፍተኛ ድምቀት ተከፍቶ ይኸው አገልግሎቱ በሰፊው ቀጥሏል።

ቤተክርስቲያናችን ከደረሰበት የእድገት አኳያ ለምዕመናኑ የሚሰጣቸውን የተለያዩ መንፈሳዊ አገልግሎቶች ይበልጥ ለማመቻቸትና ለማጠናከር ያመች ዘንድ እ ኤ አቆጣጠር በ 2000 ዓም ለመጀመሪያ ጊዜ ቤተክርስቲያኑ የሚመራበትን የመተዳደሪያ ደንብ (By-Law) አዘጋጅተን ስንጠቀምበት ቆይተናል።

ይህን መተዳደሪያ ደንብ በማሻሻል የአስተዳደር መዋቅሩን ማስተካከልና የበለጠ የተጠናከረ እንዲሆን ማድረግ አግባብና ወቅታዊ መሆኑን በመገንዘብ በምዕመናን ጠቅላላ ጉባኤ የደንብ አሻሻይ ኮሚቴ ተመርጦ ሥራውን ሲያከናውን ቆይቷል። የተመረጠው የደንብ አሻሻይ ኮሚቴ በዩናይትድ ስቴትስ የሚገኙ የተለያዩ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ኃይማኖት ተከታይ ቤተክርስቲያናት የሚተዳደሩባቸውን መተዳደሪያ ደንቦች በአገልግሎት ላይ ካለው የደብረ ገነት ቅዱስ አማኑኤል ቤተክርስቲያን መተዳደሪያ ደንብ ጋር በማገናዘብ ከተመለከተና ካጠና በኋላ እንደሚከተለው አሻሽሎ አቅርቧል።

የደብረ ገነት ቅዱስ አማኑኤል ቤተክርስቲያን ማህበረ ምዕመናን ጠቅላላ ጉባኤ በዚሁ በቀረበው ረቂቅ ላይ በተከታታይ ስብሰባዎች በሰፊው ከተወያየ በኋላ ተሻሽሎ የቀረበውን መታዳደሪያ ደንብ አጽድቆታል።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር!!!

## በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ኃይማኖት
## የደብረ ገነት ቅዱስ አማኑኤል ቤተክርስቲያን
## መተዳደሪያ ደንብ

አንቀጽ - 1 - <u>የደብረ ገነት ቅዱስ አማኑኤል ቤተክርስቲያን</u>

ሀ - በዚህ መተዳደሪያ ደንብ የተቋቋመዉ ቤተክርስቲያን በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት የደብረ ገነት ቅዱስ አማኑኤል ቤተክርስቲያን በሚል ስያሜ የሚጠራ ይሆናል። ቤተክርስቲያኑ በፔንሲልቫኒያ ሕግና ደንብ መሠረት የተቋቋመ ሕጋዊ አካል ነው።

ለ - የደብረ ገነት ቅዱስ አማኑኤል ቤተክርስቲያን ዋና መኖሪያው በፊላደልፊያ ከተማ በፔንሲልቫኒያ ይሆናል። አድራሻውም፦

| | |
|---|---|
| Ethiopian Ortodox Tewahdo Religion | የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት |
| Debre Genet Kidus Ammanuel Church | የደብረ ገነትቅዱስ አማኑኤል ቤተክርስቲያን |
| 6825-33 Greenway Avenue | 6825-33 ግሪንወይ ጎዳና |
| Philadelphia, PA 19142 | ፊላደልፊያ, ፔንስልቫኒያ 19142 |

(or) ወይም

| | |
|---|---|
| Ethiopian Orthodox Tewahdo Religion | የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት |
| Debre Genet Kidus Ammanuel Church | የደብረ ገነት ቅዱስ አማኑኤል ቤተክርስቲያን |
| P.O.Box 38590 | የፖስታ ሣጥን ቁጥር 38590 |
| Philadelpia, PA 19104 | ፊላደልፊያ, ፔንስልቫኒያ19104 |

ሐ - የደብረ ገነት ቅዱስ አማኑኤል ቤተክርስቲያን ማህተም መስቀል ያለበት ክብ ቅርጽ ሆኖ በአማርኛና በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተቀረጸ ይሆናል።

መ - የቤተክርስቲያኑ የሂሳብ ዓመት January 1 ቀን ጀምሮ December 31 ቀን የሚጠናቀቅ ይሆናል።

አንቀጽ - 2 - <u>ዓላማ</u>

ሀ - የደብረ ገነት ቅዱስ አማኑኤል ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የተቋቋመው በጌታችን በመድኃኒታችን በአምላካችን በኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርት ላይ ተመሥርቶ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ከዘመናት ተቀብላ ያቆየችውን ሥርዓተ እምነትና አምልኮት ለማካሄድና ለጸሎት አገልግሎት ነው።

ለ - በ1954 በወጣው በአሜሪካን ፌደራል መንግስት በግብር አዋጅ በሴክሽን 501 (ሲ) (3) በተመለከተው ሕግ በቁጥር 23-2860452 ተመዝግቦ ከግብር ነጻ ሆኖ ሥራውን የሚያከናውን ይሆናል።

አንቀጽ - 3 - <u>ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ጋር ስለሚኖረው ግንኙነት</u>

ሀ - እምነትን፤ ሥርዐተ አምልኮትንና ተዋህዶ ሃይማኖትን በሚመለከት የደብረ ገነት ቅዱስ አማኑኤል ቤተክርስቲያን ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የማይነጠል የቤተክርስቲያኑ ውሁድ አካል ይሆናል።

ለ - በአስተዳደር ጉዳይ ደብረ ገነት ቅዱስ አማኑኤል ቤተክርስቲያን ራሱን የቻለ ሲሆን ቤተክርስቲያኑ ከተመሠረተ ጀምሮ የያዘው የገለልተኝነት አቋም እንደተጠበቀ

ሆኖ በዚህ ደንብና አግባብ ባላቸው የፔንሲልቫኒያ ስቴት ሕጎች መሠረት ተመርጦ በሚያገለግል የአስተዳደር ጉባኤ ይመራል።

አንቀጽ -4- <u>የቤተክርስቲያኑ ተግባርና ሥልጣን</u>

ሀ- ቤተክርስቲያኑ የተቋቋመበትን ዓላማ ለማስፈጸም ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ተግባራት ያከናውናል።

1- በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት እምነት፥ ሥርዓትና ባህል መሠረት የአምልኮተ እግዚአብሔር አገልግሎት መስጠት።

2- በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነትና ሥርዓት መሠረት የሥርዓተ ቅዳሴ፥ የሥርዓተ ጥምቀት፤ የሥርዓተ ጋብቻ፤ የሥርዓተ ፍትሃትና የምክር አገልግሎት መስጠት።

3- የምዕመናንን ዕውቀት ማዳበር የሚያስችል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖትን ታሪክ፤ ባህልና ቅዱሳት መጻሀፍትን የሚመለከት ትምህርታዊ ፕሮግራም አዘጋጅቶ ማቅረብ።

4- የግእዝ፤ የዜማና የቅኔ ትምህርት የሚሰጥበት ፕሮግራም ማዘጋጀት።

5- በአካባቢው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖትን ለማጠናከር በሚደረገው ጥረት ከእህት ቤተክርስቲያናት፦ ከግብጽ፤ከሕንድ፤ ከአርመንና ከሶርያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያናት ጋር መተባበር።

ለ- የተቋቋመበትን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የደብረ ገነት ቅዱስ አማኑኤል ቤተክርስቲያን ውል የመዋዋል፤ ዕርዳታና መዋጮ የመሰብሰብን ሥልጣን ጨ ም ሮ አትራፊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 86-569 ላይ የተዘረዘረው አጠቃላይ ሥልጣን ይኖረዋል።

ሐ- የደብረ ገነት ቅዱስ አማኑኤል ቤተክርስቲያን ለትርፍ የተቋቋመ ድርጅት ባለመሆኑ ፖለቲካ ነክ በሆኑ ጉዳዮች ላይ እንዳይሳተፍ ይታገዳል።

መ- ማንኛውም የአስተዳደር ጉባኤ አባል ለቤተክርስቲያኑ የሚሰጠው አገልግሎት በበጎ ፈቃድ ስለሆነ ከቤተክርስቲያኑ ከሚገኘው ገቢ ተካፋይ አይሆንም። አንድ አባል ተግባሩን ለማከናወን የተለየ ወጪ ካወጣና ለዚሁ ደረሰኝ ካቀረበ ያወጣው ገንዘብ ይመለስለታል፤ ሆኖም ከካህናት ጉባኤ ተወክለው በአስተዳደር ጉባኤው ውስጥ የሚያገለግሉት ካህን በአስተዳደር ጉባኤ አባልነታቸው ሳይሆን በክህነት አገልግሎታቸው የሚያገኙትን አበል ወይም ድጎማ አይመለከትም።

አንቀጽ -5- <u>አባልነት</u>

የቃሉ መንፈሳዊ አግባብ እንደተጠበቀ ሆኖ ከዚህ ደንብ አፈጻጸም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት መ ሠረት በጌታችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የሚ ያምንና/የምታምን/ ዕድሜው/ዋ/ ከ18 ዓመት በላይ የሆነ ሁሉ ከዚህ በታች የተጠቀሱትን በተጨማሪ የሚ ያሟ ላ/የምታሟ ላ/ ከሆነ የደብረ ገነት ቅዱስ አማኑኤል ቤተክርስቲያን አባል ለመ ሆን ይችላል/ትችላለች/።

ሀ- ቤተክርስቲያን አዘውትሮ የሚሳተፍ/የምትሳተፍ/።

ለ- የቤተክርስቲያኑን ዓላማ ለማራመድ ለአገልግሎት ሲጠየቅ/ስትጠየቅ/ ፈቃደኛ ሆኖ/ሆና/ የሚቀርብ/የምትቀርብ/።

ሐ- የቤተክርስቲያኑን ዕድገትና ልማት የሚያራምድ/የምታራምድ/።

መ- በማህበረ ምዕመናን ጠቅላላ ስብሰባ የተወሰነውን በቤተሰብ $20 ዶላር እና በግለሰብ $10 ዶላር መዋጮ በየወሩ ለመክፈል ፈቃደኛ የሆነ/የሆነች/።

ሠ- የቤተክርስቲያኑን መተዳደሪያ ደንብ ተቀብሎ/ተቀብላ/ የሚያከብርና/የምታከብርና/ በሥራ ላይ የሚያውል/የምታውል/።

አንቀጽ -6- <u>የአባልነት መብትና ግዴታ</u>

1- መተዳደሪያ ደንቡን ተቀብሎ በተግባር ማዋል።

2- ለአስተዳደር ጉባኤ አባልነት ለመምረጥና ለመመረጥ።

3- የደብረ ገነት ቅዱስ አማኑኤል ቤተክርስቲያን አባላት ለምዕመናን ጠቅላላ ጉባኤ ለውሳኔ በሚቀርቡ ጉዳዮች ላይ ሃሳብ የማቅረብና ድምጽ የመስጠት መብት አላቸው። ሆኖም የአስተዳደር ጉባኤ አባላትንና ሌሎች ኃላፊዎችን ለመምረጥ በሚደረግ ስብሰባ ድምጽ መስጠት የሚችሉት ምርጫው ከመካሄዱ በፊት በነበሩት ስድስት ወራት የአባልነት መዋጮዋቸውን በተከታታይ ባለማቋረጥ የከፈሉ መሆን አለባቸው።

4- የደብረ ገነት ቅዱስ አማኑኤል አባላት ቤተክርስቲያኒቱ የምትሰጣቸውን አገልግሎቶች ያለክፍያ ያገኛሉ፤ ሆኖም አባላት ከሚያገኙት አገልግሎት በገዛ ፈቃዳቸው የተቻላቸውን ከመለገስ ይህ ደንብ አይገድባቸውም።

5- ማንኛውም የደብረ ገነት ቅዱስ አማኑኤል አባል ከቤተክርስቲያኑ አባላት አንድ ሶስተኛውን (1/3 ሲሶ) ማስፈረም አስከቻለ ድረስ የአባላት አስቸኳይ ስብሰባ የማስጠራት መብት አለው።

አንቀጽ -7- <u>ከአባልነት መሰረዝና በድጋሚ አባል ስለመሆን</u>

ሀ- አንድ አባል ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ኃይማኖት ሥርዓተ ትምህርት፤ ሕግ፤ ቀኖናና እምነት ተጻራሪ የሆነ ተግባር ፈጽሞ ሲገኝ እና ግብረ ገብነትን የሚቃረን ተግባር ሲያደርግ ከተገኘ በቤተክርስቲያኑ አባቶችና በአስተዳደር ጉባኤው ተመክሮ ከድርጊቱ የማይመለስ ሲሆን፤

ለ- የአባልነት ክፍያውን ያለበቂ ምክንያት ከሶስት ወራት በላይ አቋርጦ የአባልነት ክፍያውን እንዲያሟላ የጽሁፍ ማሳሰቢያ ደርሶት ቀሪ የአባልነት ክፍያውን ሳያሟላ ሲቀር ከአባልነት ይሠረዛል።

ሐ-ከላይ በንዑስ አንቀጽ (ሀ) እና (ለ) መሠረት ከአባልነት የተሠረዘ ከአባልነት የተሠረዘበትን ምክንያት አስተካክሎ ከቀረበ አንደገና ወደ አባልነት እንዲመለስ ሊፈቀድለት ይችላል።

መ-አንድ አባል አባልነቱ የተሠረዘው ከላይ በተራ ቁጥር 7(ሀ) ከተዘረዘሩት ምክንያቶች በአንዱ ከሆነ አባሉ በራሱ ፈቃድ ጉዳዩን ከደብሩ አባቶች አቅርቦ በአባቶች ተመክሮና ተዘክሮ መስተካከሉ ከተረጋገጠና አባቶች ተመልሶ አባል መሆን እንደሚችል ካረጋገጡ ወደአባልነቱ እንዲመለስ ይፈቀድለታል።

ሠ-አንድ አባል ከአባልነቱ የተሠረዘው ከላይ በ 7(ለ) በተጠቀሰው ምክንያት ከሆነ አባልነቱ እስከተሠረዘበት ጊዜ ያላሟላውን ክፍያ እንዲያሟላ ተደርጎ ወደ አባልነት እንዲመለስ ሊፈቀድለት ይችላል።

ረ- አንድ አባል ከአባልነት የሚሠረዘው ለዚሁ መነሻ የሆነውን ምክንያት በቅድሚያ እንዲያውቀው ተደርጎ ውሳኔ ከሚሰጠው አካል የበኩሉን መከላከያ አቅርቦ ከታየለት በኋላ ይሆናል።

ሰ- አንድ አባል በዚህ ደንብ መሠረት የተወሰነውን የአባልነት ክፍያ ሲከፍል ቆይቶ ከአባልነት ቢሰረዝ እስከዚያ ጊዜ ድረስ የከፈለው ክፍያ ይመለስልኝ ብሎ የመጠየቅ መብት የለውም።

አንቀጽ -8-1- <u>የአስተዳደር ጉባኤ ተግባርና ኃላፊነት</u>

የአስተዳደር ጉባኤ ተጠሪነቱ ለማህበረ ምዕመናን ጠቅላላ ጉባኤ ሆኖ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል፦

ሀ- በአንቀጽ 4ንዑስ አንቀጽ ሀ ላይ የተዘረዘሩት ተግባራት በሥራ መተርጐማቸውን ይቆጣጠራል።

ለ- መተዳደሪያ ደንቡ በሥራ መተርጐሙን ያረጋግጣል።

ሐ- የማህበረ ምዕመናን ጠቅላላ ጉባኤ የሚያሳልፋቸው ውሳኔዎች በሥራ መተርጐማቸውን ይከታተላል፤ ያረጋግጣል።

መ-ማንኛውም የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ የቤተክርስቲያኑ ሃብትና ንብረት በቤተክርስቲያኑ ስም ተመዝግቦ በአግባቡ እንዲጠበቅ አስፈላጊውን ሁሉ ያደርጋል።

ሠ- የቤተክርስቲያኑን ዓመታዊ በጀት አውጥቶ በጠቅላላ የማህበረ ምዕመናን ጉባኤ ያጸድቃል፤ በሥራ ላይም እንዲውል ያደርጋል።

ረ- የቤተክርስቲያኑን እድገት በማስመልከት የአጭርና የረዢም ጊዜ ፕላን በማውጣት ለማህበረ ምዕመናን ጠቅላላ ጉባኤ አቅርቦ ያጸድቃል፤ በተግባር መዋሉንም ይከታተላል።

ሰ- በቤተክርስቲያኑ ስም አስፈላጊ ውሎችን ይዋዋላል፤ ክስ ይመሠርታል፤ ሲከሰስም መልስ ይሰጣል። ሆኖም የሚገባው ውል ከ $10,000 /አሥር ሺህ ዶላር/ በላይ የሚያስወጣ ከሆነ በቅድሚያ ለማህበረ ምዕመናን ጠቅላላ ጉባኤ አቅርቦ ያስፈቅዳል።

የአስተዳደር ጉባኤው በቤተክርስቲያኑ ስም ተመዝግቦ የሚገኘውን ሕንፃ መሸጥ፤ መለወጥ ወይም በመያዣነት አስይዞ መበደር አይችልም። አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ግን ይህንን ጉዳይ በተመለከተ ብቻ የሚነጋገርና ውሳኔ የሚሰጥ ፤ ከ30 ቀን ያካነሰ ጊዜ በመስጠት አስቀድሞ ስለስብሰባው አጀንዳ ማስታወቂያ እንዲነገር በማድረግ በሚጠራ የአባላት ጠቅላላ ጉባኤ ላይ ጉዳዩን አቅርቦ ውይይት ከተደረገ በኋላ ከአባላት ¾ ኛው ከደገፉት በዚሁ ውሳኔ መሠረት ያስፈጽማል።

ሸ- ከቤተክርስቲያኑ የሚሰጡ ስጦታዎችን ይቀበላል፤ በአግባቡ ተመዝግበው ገቢ እንዲደረጉ ያደርጋል።

ቀ- እንደአስፈላጊነቱ ንዑሳን ኮሚቴዎችን ያቋቁማል፤ መመሪያ ይሰጣል፤ የተቋቋሙበትን ዓላማ ተግባራዊ ማድረጋቸውን ይቆጣጠራል።

በ- በክፍያም ሆነ ያለክፍያ የሚያገለግሉ ተጨማሪ ካህናትን ወይም ዲያቆናትን ለመቅጠር ወይም ለመጨመር አስፈላጊነቱ በአስተዳደር ጉባኤው ከታመነበት ወይም በካህናት ጉባኤ በኩል ከቀረበ ተገቢው ምልመላ በካህናት ጉባኤ በኩል ተሟልቶ እንዲቀርብ በማድረግ የውሳኔ ኃሳብ ሲቀርብለት ውሳኔ ይሰጣል። ሌሎች የሥራ ኃላፊነቶችን በተመለከተ ሠራተኛ መቅጠር ቢያስፈልግ ምልመላውንም ሆነ ቅጥሩን የሚፈጽመው የአስተዳደር ጉባኤው ይሆናል።

ተ- የአስተዳደር ጉባኤው ካህናት ወይም ዲያቆናት የሥራ ድክመት ወይም የዲሲፒሊን ጉድለት ማድረሳቸውን ካረጋገጠ (ምስጢራተ ቤተክርስቲያንን እና ክህነትን ከሚመለከቱ ጉዳዮች በስተቀር) እንደ አስፈላጊነቱ ምክር ይሰጣል ወይም የሥነስርአት እርምጃ ይወስዳል። የሚወሰደው እርምጃ ከሥራ መሰናበትን የሚያስከትል ከሆነ አስተዳደር ጉባኤው የሚሰጠው ውሳኔ በሁለት ሦስተኛ ድምጽ መደገፍ ይኖርበታል።

አንድ ካህን ወይም ዲያቆን ከሥራ እንዲሰናበት ከመደረጉ በፊት የፈጸመው ጥፋት ምስጢራተ ቤተክርስቲያንን ወይም ክህነትን የተመለከተ ከሆነ ጉዳዩን አስቀድሞ የካህናት ጉባኤ እንዲመረምረውና የውሳኔ ሃሳብ እንዲያቀርብ ይደረጋል። ካህኑ ወይም ዲያቆኑ ከሥራ የሚሰናበትበት ምክንያት በዝርዝር ተገልጦለት የማያምንበት ከሆነ ቅሬታውን በዚሁ ደንብ መሠረት ለሚቋቋም የአማካሪዎች ኮሚቴ አቅርቦ የማሰማት መብት አለው።

ቸ- በየስድት ወር ለሚካሄደው የማህበረ ምዕመናን ጠቅላላ ስብሰባ የሂሳብና የሥራ ክንውን ሪፖርት ያቀርባል። ቢያንስ ግን በዓመት አንድ ጊዜ ጠቅላላ ስብሰባ በመጥራት የሂሳብና የሥራ ክንውን ሪፖርት የማቅረብ ኃላፊነት አለበት።

ኀ- ይህን መተዳደሪያ ደንብ በሥራ ላይ ለማዋል አስፈላጊ የሆኑ የሥራ መመሪያዎችን ያወጣል፤ በሥራ ላይ መዋላቸውንም ያረጋግጣል።

ነ- የአስተዳደር ጉባኤው ካህናትና ዲያቆናት የሚተዳደሩበት የሥራ ደንብና መመሪያ ያወጣል። መመሪያው የአበል ክፍያን፤ ፈቃድንና አንዳንድ አስፈላጊ የሆኑ ወጪዎች የሚከፈሉበትን ሁኔታ የሚያካትት ይሆናል።

አንቀጽ -8-2- <u>የአስተዳደር ጉባኤ አባል ሆነው ማገልገል የሚፈልጉ ምዕመናን የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት ይጠበቅባቸዋል።</u>

ሀ- በፔንስልቫኒያና አካባቢው ቢያንስ ለስድስት ወራት ነዋሪ የሆነ /የሆነች/፤

ለ- በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ኃይማኖት ሥርዓት መሠረት የተጠመቀ/የተጠመቀች/ና በቤተክርስቲያኑ ውስጥ ትጉህ አባልና ተከታይ የሆነ/የሆነች/፤

ሐ- አስራ ስምንት ዓመት ወይም ከዚያ በላይ የሆነ/የሆነች/ና ማንበብና መጻፍ ጠንቅቆ/ጠንቅቃ/ የሚያውቅ/የምታውቅ/፤

መ- ቢያንስ ለ 6ወራት አከታትሎ/አከታትላ/ የደብረ ገነት አማኑኤል ቤተክርስቲያን አባልነቱን/አባልነቷን/ ክፍያ አጠናቆ/አጠናቃ/ የከፈለ/የከፈለች/ መሆን አለበት/አለባት/።

አንቀጽ -8- 3- <u>የአስተዳደር ጉባኤ አባላት ብዛት</u>

ሀ- የደብረ ገነት ቅዱስ አማኑኤል ቤተክርስቲያን ከአሥራ አንድ ያልበለጡ ከሰባት ያላነሱ የአስተዳደር ጉባኤ አባላት ይኖሩታል።

ለ- ይህ የአስተዳደር ጉባኤ አባላት ቁጥር እንደአስፈላጊነቱ በማህበረ ምዕመናን ጠቅላላ ጉባኤ ሊቀነስ ወይም ሊጨመር ይችላል።

ሐ- አስተዳደር ጉባኤው የአባላቱን ቁጥር ያለምዕመናን ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ መቀነስ ወይም መጨመር አይችልም።

መ- አስተዳደር ጉባኤው አንድ ከምዕመናን መካከል የተመረጠ የአስተዳደር ጉባኤ አባልን ከአገልግሎት ማስወገድ የሚችለው ጉዳዩ ለማህበረ ምዕመናን ጠቅላላ ጉባኤ ቀርቦ ውሳኔ ካገኘ በኋላ ብቻ ነው።

ሠ- የካህናት ጉባኤ መርጦ የሚመድበው ካህን የአስተዳደር ጉባኤው አባል ይሆናል። የካህናት ጉባኤ መርጦ የሚመድበው የአስተዳደር ጉባኤ አባል ካህን እንደሌሎቹ የአስተዳደር ጉባኤ አባላት ሁሉ የሚያገለግለው ለሁለት ዓመታት ሆኖ የካህናት ጉባኤ ካመነበት እንደገና ለሌላ ሁለት ዓመት አገልግሎት ሊመረጥ ይችላል፤ ሆኖም ለሦስተኛ ጊዜ የአስተዳደር ጉባኤ አባል ሆኖ ከመመረጡ በፊት አንድ የምርጫ ዘመን ማሳለፍ ይኖርበታል።

አንቀጽ -9- <u>የካህናት ጉባኤ መርጦ ከሚመድበው ካህን፥ የሰንበት ት/ቤት ክፍል መርጦ ከሚልከው ተወካይ እና በመሥራች አባልነታቸው በቋሚ አባልነት እንዲያገለግሉ ከተፈቀደላቸው ወ/ሮ የሺ ዳዲ በስተቀር ማንኛውም የአስተዳደር ጉባኤ አባላት በምዕመናን እንደሚከተለው ይመረጣሉ፦</u>

ሀ- <u>አስመራጭ ኮሚቴ</u>

1- የቤተክርስቲያኑ ማህበረ ምዕመናን ጠቅላላ ስብሰባ አምስት አባላት ያሉት አስመራጭ ኮሚቴ ያቋቁማል። የአስመራጭ ኮሚቴ ተመራጮች ከመካከላቸው ሊቀመንበርና ጸሐፊ ሆነው የሚያገለግሉ አባላትን ይመረጣሉ፤ የአሠራር ሥነስርዓት ያወጣሉ።

2- የአስተዳደር ጉባኤ አባላት ምርጫ ከሚከናወንበት ዕለት 3 ወር (ዘጠና ቀናት) አስቀድሞ አስመራጭ ኮሚቴ ይቋቋማል።

3 - የአገልግሎት ዘመናቸውን በሚፈጽሙ የአስተዳደር ጉባኤ አባላት ምትክ ምርጫ የሚከናወነው በጥር ወር ወስጥ በመጨረሻው እሁድ /Last Sunday in January/ ይሆናል።

4 - አስመራጭ ኮሚቴው ምዕመናን የአስተዳደር ጉባኤው አባል ሆነው ሊያገለግሉ ብቃት አላቸው ብለው የሚያምኑባቸውን አባላት የስም ጥቆማ ይጠይቃል። ኮሚቴው ጥቆማው ከአንድ ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ እንደሚጠናቀቅ ለምዕመናን በቅድሚያ ያሳውቃል። በዚህ ጊዜ ውስጥ ኮሚቴው ጥቆማውን ማጠናቀቅ ካልቻለ የጊዜ ገደቡ እንዲራዘም ለምዕመናን ጠቅላላ ጉባኤ ጥያቄ በማቅረብ ያስፈቅዳል።

5 - የጥቆማው ጊዜ ገደብ ካለፈ ከሁለት ሳምንት በኋላ አስመራጭ ኮሚቴው ተጠቋሚዎችን ለምዕመናን ያሳውቃል፤ በዚሁ ዕለት ምርጫው የሚከናወንበትን ቀን በይፋ ያሳውቃል። ምርጫው በሚከናወንበት ዕለት እጩዎች ራሳቸውን ለምዕመናን እንዲያስተዋውቁ ይደረጋል ወይም አስመራጭ ኮሚቴው ስለ ተጠቋሚዎቹ አጠር ያለ መግለጫ ይሰጣል።

6 - አንድ ተጠቋሚ ለምርጫ ለመቅረብ ፈቃደኛነቱን ለአስመራጭ ኮሚቴው ካሳወቀ በኋላ በተለያየ ምክንያት የምርጫ ስብሰባ በሚደረግበት ዕለት ሳይገኝ ቢቀር አስመራጭ ኮሚቴው በሚሰጠው አጠር ያለ መግለጫ መነሻ ምዕመናን በሚሰጡት ድምጽ አሸናፊ ከሆነ በዕለቱ አለመገኘቱ ከምርጫው አሸናፊነት አያግደውም።

7 - በማህበረ ምዕመናን ጠቅላላ ስብሰባ ላይ ምርጫው ተካሂዶ ከፍተኛ ድምጽ ያገኙ እጩዎች የአስተዳደር ጉባኤው አባላት ሆነው እንዲሠሩ ይወሰናል። በእለቱ በተሰጠው ድምጽ ከተመራጭ እጩዎች በመቀጠል ከፍተኛ ድምጽ ያገኙት እጩዎች በተጠባባቂነት ተይዘው ይቆያሉ።

8 - አስመራጭ ኮሚቴው ምርጫው በተጠናቀቀ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ዘመናቸውን ፈጽመው በሚለቁትና በተተኪዎች መካከል የሥራ ርክክብ መደረጉን ያረጋግጣል።

ለ - <u>የአስተዳደር ጉባኤ አባላት የአገልግሎት ዘመን</u>

የማንኛውም የአስተዳደር ጉባኤ አባል የአገልግሎት ዘመን ለሁለት ዓመት ይሆናል። ሆኖም አንድ የአስተዳደር ጉባኤ አባል የአገልግሎት ዘመኑን ከፈጸመ በኋላ ለሌላ ተጨማሪ የአገልግሎት ዘመን ሊመረጥ ይችላል። ከሁለት ተከታታይ የአገልግሎት ዘመን በኋላ ለመመረጥ ግን ቢያንስ ሁለት ዓመት መጠበቅ ይኖርበታል።

ሐ - <u>አከስተዳደር ጉባኤ አባልነት ስለመልቀቅ</u>

ማንኛውም የአስተዳደር ጉባኤ አባል በአገልግሎት ሊቀጥል የማይችልበት ምክንያት ካጋጠመው ሁኔታውን በጽሑፍ ለአስተዳደር ጉባኤው በማቅረብ ራሱን ከአገልግሎት ማግለል ይችላል።

መ - <u>ከአስተዳደር ጉባኤ አባልነት ስለመወገድ</u>

አንድ የአስተዳደር ጉባኤ አባል በሚከተሉት ምክንያቶች ከአባልነት ሊወገድ ይችላል፦

1- በዚህ መተዳደሪያ ደንብ በአንቀጽ 5 ላይ በተደነገገው መሠረት ከአንድ የደብረ ገነት ቅዱስ አማኑኤል ቤተክርስቲያን አባል ምዕመን የሚጠበቅ ግዴታውን አሟልቶ ካልተገኘ፤

2- የደብረ ገነት ቅዱስ አማኑኤል ቤተክርስቲያንን ሕልውና የሚጻረር ተግባር ፈጽሞ ከተገኘ ይኸውም፦

ሀ- ምዕመናንን በፖለቲካ፤ በዘርና በተለያዩ ምክንያቶች ለመከፋፈል የሞከረ፤

ለ-ወንጀል ፈጽሞ የተፈረደበት ሲሆንና የፈጸመው ወንጀል በቤተክርሲቲያኒቱ ሕልውና ላይ የሚንጸባረቅ ከሆነ፤

3- የአስተዳደር ጉባኤውን የሥራ እንቅስቃሴ የሚያደናቅፍ ተግባር በተደጋጋሚ ሆን ብሎ ከፈጸመ፤

4- የቤተክርስቲያኑን ንብረትና ገንዘብ ያለአግባብ ያባከነና እንዲባክን ተባባሪ የሆነ፤ ከአስተዳደር ጉባኤ አባልነቱ ይወገዳል።

ሠ- አንድ የአስተዳደር ጉባኤ አባል ከኃላፊነቱ ከመወገዱ በፊት የፈጸመው ጥፋት ተገልጦለት የበኩሉን ማስረጃ በማቅረብ የመከላከል መብት ይኖረዋል።

ረ- <u>የጎደለ ቦታ</u>

በአስተዳደር ጉባኤው ውስጥ የጎደለ ቦታ የሚኖረው አንድ የአስተዳደር ጉባኤ አባል በዚህ ደንብ መሰረት በገዛ ፈቃዱ/ዷ/ አገልግሎቱ/ቷ/ን ሲያቋርጥ/ስታቋርጥ/፤ ከአገልግሎት የሚወገድበት/የምትወገድበት/ ተግባር ፈጽሞ/ፈጽማ/ ከአገልግሎት እንዲወገድ/እንድትወገድ/ ሲወሰንበት/ሲወሰንባት/፤ ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ/ስትለይ/ ወይም በማህበረ ምዕመናን ውሳኔ የአስተዳደር ጉባኤ አባላት ቁጥር እንዲጨምር ሲወሰን ነው። በዚህ ሁኔታ ክፍት ቦታ ሲፈጠር ባለፈው ምርጫ ከፍተኛ ድምጽ አግኝተው በተጠባባቂነት ከተያዙ እጩዎች መካከል የአባሉን/የአባሏን/ የአገልግሎት ዘመን እንዲፈጽሙ ይጠየቃሉ። ከፍተኛውን ድምጽ ያገኙት እጩ ፈቃደኛ ሆነው ከተገኙ የአስተዳደር ጉባኤ አባልነታቸውን በጽሑፍ አረጋግጦ ይሰጣቸዋል፤ ለምዕመናንም በማስታወቂያ ይገለጣል። የጎደሉት አባላት ቁጥር ከሁለት በላይ ከሆነ ወይም የቀረው የአገልግሎት ዘመን ከአንድ ወር ከበለጠ እና ተጠባባቂ እጩዎች ፈቃደኛ ሆነው ካልተገኙ አስቸኳይ ምርጫ ይከናወናል።

አንቀጽ -10- <u>የአስተዳደር ጉባኤ ስብሰባዎች</u>

1- <u>የስብሰባ ቦታ</u>

የአስተዳደር ጉባኤው ስብሰባዎች በፊላደልፊያ ከተማ ይደረጋሉ። አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝና የቴክኖሎጂው አቅም ሲፈቅድ አባላት በአካል ካልተገኙ በስልክ የስብሰባው ተካፋይ መሆን ይችላሉ።

2- <u>መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባ</u>

አስተዳደር ጉባኤው በየወሩ መደበኛ ስብሰባ ያደረጋል። አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ የአስተዳደር ጉባኤው ሊቀመንበር ወይም ከጉባኤው አባላት አምስቱ ከጠየቁ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል። ስብሰባውን የሚመራው የአስተዳደር ጉባኤው ሊቀመንበር ይሆናል። የስብሰባው አስፈላጊነት በቅድሚያ ለአባላት መገለጥ ይኖርበታል።

3 - <u>ምልዐተ ጉባኤ</u>

የፔንስልቫኒያን ሕግ የማይቃረን እስከ ሆነ ድረስ ከአስተዳደር ጉባኤው አባላት 50% + 1 (ከግማሽ በላይ) ከተገኙ ምልዐተ ጉባኤ ይሆናል። በተጠራው ስብሰባ ላይ ምልዐተ ጉባኤ ካልሞላ ስብሰባው ለሌላ ጊዜ ይተላለፋል። ሆኖም በሚቀጥለው የስብሰባ ቀን በሚገኙት አባላት ብቻ ምልዐተ ጉባኤ እንደተሟላ ተቆጥሮ አስፈላጊው ውሳኔ ሊተላለፍ ይችላል።

4 - <u>ቃለ ጉባኤ</u>

የአስተዳደር ጉባኤው ፀሐፊ የአስተዳደር ጉባኤ ስብሰባዎችን ቃለ ጉባኤ በጽሑፍ አዘጋጅቶ ያቀርባል። የተዘጋጀው ቃለ ጉባኤ በሚቀጥለው ስብሰባ ላይ በንባብ ይሰማል፤ በቃለ ጉባኤው ላይ ለውጥ መደረግ ካለበት ይኸው ለውጥ በዕለቱ ስብሰባ ቃለ ጉባኤ ላይ እንዲካተት ይደረጋል። ሁሉም ቃለ ጉባኤዎች በሊቀመንበሩና በጸሐፊው ይፈረማሉ።

5 - <u>በድምጽ ብልጫ ውሳኔዎችን ስለማሳለፍ</u>

ማንኛውም የአስተዳደር ጉባኤው ውሳኔ በድምጽ ብልጫ ይወሰናል፤፤ በአብዛኛው ድምጽ የተላለፈ ውሳኔ ተፈጻሚ ይሆናል።

አንቀጽ -11- <u>የደብረ ገነት ቅዱስ አማኑኤል ቤተክርስቲያን የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት</u>

የደብረ ገነት ቅዱስ አማኑኤል ቤተክርስቲያን የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለአስተዳደር ጉባኤ ሆኖ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል፦

1 - የቤተክርስቲያኑን የዕለት ከዕለት ተግባር የሚያከናውን አምስት አባላት ያሉበት የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ይኖራል።

2 - የቤተክርስቲያኑን ዓመታዊ በጀት፤ እቅድና ፕሮግራም እያዘጋጀ ለአስተዳደር ጉባኤው ያቀርባል፤ ጉባኤው ያጸደቀውንም በሥራ ላይ እንዲውል ለምህበረ ምዕመናን ውሳኔ ያቀርባል፤ ሲጸድቅም በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል።

3 - በአስተዳደር ጉባኤው ለተቋቋሙ ልዩ ልዩ የሥራ ክፍሎች መመሪያ ይሰጣል፤ ሥራቸውን ያስተባብራል፤ ይቆጣጠራል፤ ስለ ሥራቸውም ተገቢውን ሪፖርት በየጊዜው ማቅረባቸውን ይከታተላል።

4 - የቤተክርስቲያኑ የሂሳብና የንብረት መዛግብት በሥርዓት መያዛቸውን ይቆጣጠራል።

5 - ከተለያዩ የገንዘብ ማሰባሰቢያ ምንጮች ለቤተክርስቲያኑ የሚበረከት ገቢ ሁሉ በአግባቡ መሰብሰቡንና በወቅቱ ባንክ ገቢ መደረጉን ያረጋግጣል።

6 - የሥራ እንቅስቃሴውን በሚመለከት በዓመት ሁለት ጊዜ ለአስተዳደር ጉባኤው ሪፖርት ያቀርባል።

7 - የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት የተመደቡበትን ሥራ ከመጀመራቸው በፊት እንደ አንድ ልብ መካሪ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ ሆነው ቤተክርስቲያኑንና አባል ምዕመናንን ለማገልገል በአስተዳደር ጉባኤው ፊት ቃል ይገባሉ፤ ከቤተክርስቲያኑ መንፈሳዊ አባትም ቃለ ቡራኬ ይቀበላሉ።

8 - የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው አባላት፦ የአስተዳደር ጉባኤው ሊቀመንበር፤ ምክትል ሊቀመንበር፤ ፀሐፊ፤ ገንዘብ ያዥና ሂሳብ ሹም ናቸው።

አንቀጽ -12- <u>የካህናት ጉባኤ</u>

"እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ፤ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችሁአቸው ያዘዝሁአችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችሁአቸው ደቀመዛሙርት አድርጓቸው ብሎ እግዚአብሔር አምላክ ለሐዋርያት በነገራቸው ቃል መሠረት" ማቴ 28፥18

የካህናት ጉባኤ ተጠሪነቱ ለቤተክርስቲያኑ የአስተዳደር ጉባኤ ሆኖ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል፦

1 - የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ኃይማኖት ዕምነትና ሥርዓተ አምልኮ በሚገባ መከናወኑን የመቆጣጠር፤ በሥርዓት እንዲካሄድ የማድረግ፤ የቅዳሴው ሥርዓት፤ የሥብከተ ወንጌሉ አሰጣጥና በጠቅላላው መንፈሳዊ አገልግሎቱ ትክክለኛውን የኃይማኖታችንን ሥርዓት ይዞ እንዲሄድ ያደርጋል።

2 - ለቤተክርስቲያኑ አገልግሎት መስጫ፤ ለሥርዓተ አምልኮትና ለኃይማኖት ሥራዎች የሚያስፈልጉ ንዋየ ቅዱሳት እንዲሟሉለት ጥያቄውን ለአስተዳደር ጉባኤው ያቀርባል።

3 - ለቤተክርስቲያኑ በስለት መልክ ገቢ የተደረጉ ንዋየ ቅዱሳትን በአግባቡ በመያዝ ለአገልግሎት አስፈላጊ ያልሆኑትን በመለየት በየስድስት ወር ለአስተዳደር ጉባኤው ውሳኔ ያቀርባል።

4 - ካህናት የንስሐ ልጆቻቸውን ከክህደትና ከኑፋቄ ልማድና ግብር ለመጠበቅ ከትምህርት ክፍሉ ጋር ጥናት በማድረግ የወንጌል ትምህርት እንዲሰጣቸው ያደርጋል።

5 - አስተዳዳሪው፣ ቄሰ ገበዙ፣ መሪ ጌታው፣ ሊቀጠበብቱ፣ ቀኝ ጌታው፣ ግራ ጌታው፣ አጋፋሪው፣ ሊቀዲያቆኑ፣ ዲያቆናት፤ መዘምራን፤ ሰባኪዎችና ሌሎችም የቤተክርስቲያን አገልጋዮች በሰዓቱ በቦታው ተገኝተው የተመደቡበትን የአገልግሎት ኃላፊነት መፈጸማቸውን ይቆጣጠራል።

6 - በሕገ ቤተክርስቲያን መሠረት ልዩ ልዩ መንፈሳዊ አገልግሎት ለምዕመናን ሁሉ በእኩልነትና በትክክል እንዲዳረስ ያደርጋል።

7- መስበክ፤ ማጥመቅ፤ ቀድሶ ማቁረብ፤ ናዝዞ ማሰናበት፤ በአጠቃላይ አማንያን በኃይማኖት እንዲጸኑና በሥነ ምግባር እንዲጎለምሱ ማድረግ የካህናት ግዴታ መሆኑን ያሳውቃል።

8- በተቻለ መጠን የታመሙትን፤ የተቸገሩና ያዘኑትን መጎብኘትና ማጽናናት የካህናት ግዴታ መሆኑን ያሳውቃል።

9- ምዕመናን በሰንበትም ሆነ በአበይት በዓላት ቀን ልጆቻቸውን ይዘው ወደ ቤተክርስቲያን በመምጣት ክርስትናቸውንና ሥርዓቱን እንዲማሩና እንዲያውቁ ፥ ምዕመናን የሰበካ ጉባኤ አባላት እንዲሆኑ፣ አባላ የሆኑ ደግሞ ተግተው የአባልነት ግዴታቸውን እንዲወጡ ያበረታታል።

10- የኢትዮጵያ ተዋህዶ ሃይማኖት እምነት ተከታይ ያልሆኑ ነገር ግን እምነቱንና ቀኖናውን ተምረው ክርስቲያን መሆን የሚፈልጉ ሰዎች ጥያቄ ሲያቀርቡ ካህናቱ ሃይማኖቱንና ሥርዓቱን በማስተማር ካሳመኗቸው በኋላ እንዲጠመቁ ይደረጋል፤ ጥያቄው መፈጸሙንም ይቆጣጠራል።

11- የሰንበት ትምህርት ቤት ክፍል መንፈሳዊ አገልግሎትና እንቅስቃሴን በተመለከተ የካህናቱ ጉባኤ ኃላፊነት አለበት። ከሰንበት ትምህርት ቤት ውስጥ ከዲቁና ከሰባኪነትና ከተለያዩ መንፈሳዊ አገልግሎት እንዲበቁ የማስተማርና የቤተክርስቲያናቸውን ስርዓት በአጠቃላይ አምልኮቱን እንዲያውቁ ማድረግ የካህናቱ ሃላፊነት ስለሆነ በደብሩ ማህበረ ምዕመናን ውስጥ ያሉትን ወጣቶች በማሰባሰብና በማደራጀት ሃይማኖታቸውን እንዲያውቁና እንዲማሩ ያደርጋል።

12- ከአገልግሎት የሚያስፈልግ በጀት እንዲመደብና እንዲፈቀድ ዝርዝሩን ከአስተዳደር ጉባኤ ያቀርባል።

13- የካህናት ጉባኤ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት እምነትና ስርዓት ውጭ የሆኑ መጻሕፍት፤ ልዩ ልዩ ፅሁፎች፤ወይም የስብከትና የመዝሙር ሲዲዎች በቤተክርስቲያኑ ቅጥር ግቢ ከምዕመናኑ እንዳይሰራጩ ጥብቅ ክትትል ያደርጋል፤ ይቆጣጠራል።

14- ክህነታቸው፤ ምንኩስናቸው ወይም ድቁናቸው በአግባቡ ሳይረጋገጥ የክህነት ወይም የድቁና አገልግሎት እንዳይሰጡ በጥብቅ ይቆጣጠራል።

15- በቃል ኪዳንና በቅዱስ ቁርባን በተጋቡ ባልና ሚስት የሚቀርቡ ክሶችን ይመለከታል፤ አስፈላጊውን መንፈሳዊ ምክር በመስጠት ችግራቸውን እንዲፈቱ ያስተምራል፣ ይመክራል።

16- የአስተዳደር ጉባኤው በዓመት ሁለት ጊዜ የሥራ ሪፖርት በሚያቀርብበት ጊዜ የካህናት ጉባኤም በእነርሱ በኩል የተከናወኑ ተግባራት አብረው ተጠቃለው እንዲቀርቡ ለማድረግ ሪፖርቱን ለአስተዳደር ጉባኤው አስቀድሞ ያቀርባል።

አንቀጽ-13- <u>የአስተዳደር ጉባኤ ሊቀመንበር ተግባርና ኃላፊነት</u>

1- የምዕመናንን አጠቃላይ ስብሰባ፤ የአስተዳደር ጉባኤውንና የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴውን ስብሰባዎች በሊቀመንበርነት ይመራል።

2- በምዕመናን አጠቃላይ ጉባኤ ወይም በአስተዳደር ጉባኤው በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ ቤተክርስቲያኑን በመወከል ውሎችን ይዋዋላል።

3- ምስጢራተ ቤተክርስቲያንን ከሚመለከቱ ጉዳዮች በስተቀር የአስተዳደር ጉባው ሊቀመንበር በዚህ ደንብ ወይም በዚህ ደንብ መሠረት በሚወጡ ደንቦች የቤተክርስቲያኑን ሥራዎች በኃላፊነት ይመራል፤ ያስተባብራል፤ ተግባራዊነታቸውንም ይቆጣጠራል።

4- ከልደትና ከጋብቻ በሚሰጡ የምስክር ወረቀቶች ላይ አገልግሎቱን የፈጸመው ካህን እንዲጠቀስ ተደርጎ የደብሩ አስተዳዳሪ እንዲፈርም ሲደረግ ከሌሎች አገልግሎቶች በሚሰጡ ሰርቲፊኬቶች ላይ ግን ከደብሩ አስተዳዳሪ ጋር በመሆን ይፈርማል።

5- የደብረ ገነት ቅዱስ አማኑኤልን ገንዘብ ከማንቀሳቀስ በቼክ ላይ እንዲፈርሙ ከሚወከሉ አባላት አንዱ ይሆናል።

6- የደብረ ገነት ቅዱስ አማኑኤልን አስተዳደር በተመለከተ ሕጋዊ ተወካይ /spoksperson/ ይሆናል።

7- ከካህናት ጉባኤ ጋር በመመካከር ደብረ ገነት አማኑኤል የተቋቋመበትን ደንብና በዚህ ደንብ መሠረት የሚወጡ መመሪያዎችን በመከተል የሰብከተ ወንጌል፤ የትምህርት፤ የወጣቶች መንፈሳዊ ማህበርና ሌሎችም እንዲቋቋሙና እንዲስፋፉ ተገቢውን ጥረት ያደርጋል፤ አስፈላጊነታቸው የታመነባቸውን ሌሎች ንዑሳን ኮሚቴዎች እንዲቋቋሙ ያበረታታል።

8- ከቤተክርስቲያኑ በሚወጡ ደብዳቤዎች ላይ ይፈርማል።

አንቀጽ -14- <u>የአስተዳደር ጉባኤው ም/ሊቀመንበር ተግባርና ኃላፊነት</u>

1- ተጠሪነቱ ለአስተዳደር ጉባኤው ሊቀመንበር ሆኖ ም/ሊቀመንበሩ የአስተዳደር ጉባኤው ሊቀመንበር በሌለበት ጊዜ የአስተዳደር ጉባኤውን፤ የማህበረ ምዕመናንን ጠቅላላ ጉባኤና የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴውን ስብሰባዎች በሰብሳቢነት ይመራል።

2- ሊቀመንበሩ በሌለበት ጊዜ ሁሉ የሊቀመንበሩን ተግባራት ያከናውናል።

3- የአስተዳደር ጉባኤው ሊቀመንበር ወይም የአስተዳደር ጉባኤው ሲወክለው ሌሎች ተጨማሪ ተግባራትን ያከናውናል።

አንቀጽ -15- <u>የአስተዳደር ጉባኤው ፀሐፊ ተግባርና ኃላፊነት</u>

የአስተዳደር ጉባኤው ፀሐፊ ተጠሪነቱ ለአስተዳደር ጉባኤው ሊቀመንበር ሆኖ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል፦

1- የአስተዳደር ጉባኤ፤ የማህበረ ምዕመናን ጠቅላላ ጉባኤና የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴውን ስብሰባዎች
ቃለ ጉባኤ ይይዛል። ቃለ ጉባኤው በሚቀጥለው ስብሰባ ተነቦ መጽደቁን ያረጋግጣል፤ ከሊቀመንበሩ ጋርም ይፈርማል።

2- በአስተዳደር ጉባኤው የሚወሰኑ ውሳኔዎች ለሚመለከታቸው ክፍሎች እንዲደርሱ ያደርጋል።

3- የቤተክርስቲያኑን ማኅተም፤ ዋና ዋና ሰነዶችና መዛግብት እንዲሁም የፖስታ ሳጥን ቁልፍ ይይዛል።

4- ከአስተዳደር ጉባኤው ሊቀመንበር ጋር በመመካከር መደበኛና አስቸኳይ የማህበረ ምዕመናን ጉባኤን፤ የአስተዳደር ጉባኤንና የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ስብሰባዎችን ቦታ፤ ቀንና ሰዓት ቀደም አድርጎ ለሚመለከታቸው ያሳውቃል።

5- ለቤተክርስቲያኑ የሚመጡ ወይም ከቤተክርስቲያኑ የሚወጡ ደብዳቤዎችን ከፋይላቸው ጋር በማያያዝ ለሚመለከተው ክፍል ቀርበው ውሳኔ እንዲሰጥባቸው ያደርጋል፤ ከውሳኔ በፊትም ሆነ በኋላ ደብዳቤዎች በጥንቃቄ በመዝገብ መያዛቸውን ያረጋግጣል።

6- ከአስተዳደር ጉባኤው ሊቀመንበር ወይም ም/ሊቀመንበር ጋር በመመካከር በየጊዜው ለሚደረጉ ስብሰባዎች አጀንዳዎችን ያዘጋጃል፤ ከሊቀመንበሩና ከሌሎችም የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ጋር በመተባበር ዓመታዊ የሥራ ሪፖርት ያዘጋጃል።

7- የቤተክርስቲያኑን አባላት መዝገብ ይይዛል፤ የሚሰጠውን መመሪያ በመከተል መታወቂያ ወረቀት እያዘጋጀ ይሰጣል፤ በወቅቱ መታደሱንም ይከታተላል።

8- ከአስተዳደር ጉባኤው ሊቀመንበርና ከቤተክርስቲያኑ አስተዳዳሪ ጋር በመመካከር የልደት፤ የጥምቀት፤ የጋብቻና የሙታን መዛግብትና ማስረጃዎች ያዘጋጃል፤ ለሚመለከታቸው አባላት መሰጠታቸውንና በማህደር መቀመጣቸውን ያረጋግጣል።

9- ከሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የሚሰጡትን ተጨማሪ ተግባራት ያከናውናል።

አንቀጽ -16- <u>የምክትል ፀሐፊ ተግባርና ኃላፊነት</u>

ምክትል ፀሐፊው ዋና ፀሐፊው በሌለበት ጊዜ ሁሉ የዋና ፀሐፊውን ሥራ ተክቶ ይሠራል፥ በተጨማሪም የመዝገብ ቤት ክፍሉን ሥራ በኃላፊነት ያከናውናል፣ እንዲሁም ከአስተዳደር ጉባኤ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

አንቀጽ -17- <u>የገንዘብ ያዥ ተግባርና ኃላፊነት</u>

ገንዘብ ያዡ ተጠሪነቱ ለአስተዳደር ጉባኤው ሊቀመንበር ሆኖ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል፦

1- ከምዕመናንና ከተለያዩ የገቢ ምንጮች ለቤተክርስቲያኑ የሚገባውን ገንዘብ ሕጋዊ ደረሰኝ በመስጠት ይቀበላል።

2- ማንኛውንም ለቤተክርስቲያኑ የተሰበሰበ ገንዘብ ከሦስት የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ በቤተክርስቲያኑ ስም በተከፈተ የባንክ ሂሳብ ውስጥ አስገብቶ ደረሰኙን ይይዛል፤ ኮፒም ለሂሳብ ሹሙ ያስረክባል።

3- የቤተክርስቲያኑን ገቢና ወጪ ለቁጥጥር በሚያመች ሁኔታ እየመዘገባ ያስቀምጣል።

4- ገንዘብ ነክ ሰነዶችንና ቼኮችን ይይዛል፤ የወጪ ማዘዣ በአስተዳደር ጉባኤው ሊቀመንበር ተፈርሞ በሂሳብ ሹሙ ተረጋግጦ ሲደርሰው ወጪ ያደርጋል፤ ኃላፊነት ከተሰጣቸው የአስተዳደር ጉባኤ አባላት ጋር በቼክ ላይ ይፈርማል።

5- የቤተክርስቲያኑን የምጽዋትና ስለት ማከማቻ ሳጥን ቁልፍ ከሚይዙት አንዱ ይሆናል፤ ከፍተኛ ግምት ያላቸው ሰነዶች የሚቀመጡበትን የባንክ ሣጥን (safety Box) ቁልፍ ይይዛል።

6- ለቤተክርስቲያኑ አገልግሎት በሥራ አመራር ኮሚቴው ተዘጋጅተው በአስተዳደር ጉባኤው የጸደቁ ወጪዎችን በደረሰኝ ወጪ ያደርጋል።

7- በየወሩ መጨረሻ ገቢና ወጪውን እንዲሁም በባንክ ያለውን ገንዘብ ከሂሳብ ሹሙ ጋር በመሆን ያመሳክራል፤ መተማመኛም ይፈርማል።

8- የአስተዳደር ጉባኤው አባላት፤ የሂሳብ ሹሙና የውጭ ኦዲተሮች ሰነዶችንና መዛግብት በማንኛውም ጊዜ ለመመልከት ቢፈልጉ በመስጠት ይተባበራል።

9- የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የሚሰጠውን ሌሎች ተጨማሪ ተግባራት ያከናውናል።

## አንቀጽ -18- <u>የሂሳብ ሹም ተግባርና ኃላፊነት</u>

የሂሳብ ሹሙ ተጠሪነቱ ለአስተዳደር ጉባኤው ሊቀመንበር ሆኖ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል፦

1. የቤተክርስቲያኑን ገቢና ወጪ በመደበኛ መዝገብ ላይ እያሰፈረ በየወሩ ከገንዘብ ያዡ ጋር በማመሳከር ትክክለኛነቱን ያረጋግጣል፤ ይህኑንም ለቤተክርስቲያኑ የአስተዳደር ጉባኤ ሊቀመንበር በየወሩ ሪፖርት ያደርጋል።
2. ከእያንዳንዱ አባል ወርሃዊ ክፍያ፤ ከሙዳዬ ምጽዋት፤ ከስለት፤ ለልዩ ልዩ አገልግሎቶች ከሚፈጸሙ ክፍያዎች፤ ለገቢ ማኀልበቻ ታስበው ከሚከናወኑ እንቅስቃሴዎችና ከበጐ አድራጊዎች የሚገኙ ገቢዎችን በየርእሳቸው መዝግቦ ይይዛል።

3. ከአስተዳደር ጉባኤው ሊቀመንበርና ከጸሐፊው ጋር በመሆን በጀት ያዘጋጃል፤በአስተዳደር ጉባኤውና በማህበረ ምዕመናን ጉባኤ ሲፈቀድ በትክክል ተግባራዊ መሆኑን ይከታተላል።

4. በቤተክርስቲያኑ ስም የተሰበሰበ ገንዘብ በዚህ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት በወቅቱና በአግባቡ በቤተክርስቲያኑ ስም በተከፈተው የባነክ ሂሣብ ገቢ መሆኑን ያረጋግጣል።

5. የገንዘብ አያያዝ ሥራዎች በትክክል መከናወናቸውን፤ ማናቸውም ወጪ በወጪ ማዘዣ ከተፈቀደውና በአስተዳደር ጉባኤው ወይም በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ውሳኔዎች ከጸደቀው ጣሪያ በላይ አለመሆኑንና ወጪው ከበጀት ጋር የተገናዘበ መሆኑን ይከታተላል።

6. ተከፋይ አዳዎች በወቅቱ መከፈላቸውን ያረጋግጣል።

7. ውስጣዊ የመቆጣጠሪያ መንገዶችን በመቀየስ የቤተክርስቲያኑ ገንዘብና ንብረት እንዳይባክን፤ ከአያያዝ ጉድለት የተነሳ እንዳይበላሽ አስፈላጊውን ጥበቃና ቁጥጥር ከማድረግ ባሻገር አስተማማኝ የሂሳብና የንብረት አያያዝ ዘዴ የመተከምና በሥራም ላይ የማዋል ኃላፊነት አለበት።

8. የባንክ ሂሳቡ በወቅቱ መታረቁን ያረጋግጣል።

9. ከአስተዳደር ጉባኤውና ከሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው የሚሰጡትን ተጨማሪ ተግባራት ያከናውናል።

አንቀጽ -19- <u>የንብረት ክፍል ኃላፊ ተግባርና ኃላፊነት</u>

የንብረት ክፍል ኃላፊው ተጠሪነቱ ለአስተዳደር ጉባኤው ሊቀመንበር ሆኖ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል፦

1- ምስጢራዊ ከሆኑ ንዋየ ቅዱሳት በስተቀር የቤተክርስቲያኑን የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረት በዘመናዊ ንብረት አያያዝ መዝገቦ ይይዛል።
2- አላቂ የሆኑ ዕቃዎች በአግባቡ ለአገልግሎት መዋላቸውን ያረጋግጣል። ከሂሳብ ሹሙ ጋር በመመካከር መተካት ያለባቸው በወቅቱ መተካታቸውን ያረጋግጣል።
3- የቆዩና አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶች ተመዝግበው የሚሸጡ ከሆኑ እንዲሸጡ፤ ለሽይጭ የማይበቁ ከሆኑ ደግሞ በአግባቡ ከመዝገብ እንዲወጡ በማድረግ እንዲጣሉ ያደርጋል።
4- የቤተክርስቲያኑን ሕንፃና ቅጥር ግቢ በመቆጣጠር ጥገና የሚያስፈልግ ሲሆን ከውሳኔ ኃሳብ ጋር ለአስተዳደር ጉባኤው ማቅረብ፦ በጽዳት መጠበቃቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል።
5- በኪራይም ሆነ ከተከያየ አገልግሎት የሚወጡ ማናቸውንም የቤተክርስቲያኑ ንብረቶች በአግባቡ መውጣትና መግባታቸውን ያረጋግጣል።
6- እንዲሁም ከአስተዳደር ጉባኤ ሊቀመንበር የሚሰጡትን ተጨማሪ ተግባራት ያከናውናል።

አንቀጽ -20- <u>የቤተክርስቲያኑ መንፈሳዊ አስተዳዳሪ ተግባርና ኃላፊነት</u>

የቤተክርስቲያኑ መንፈሳዊ አስተዳዳሪ ሥልጣነ ክህነት ያለው ቀሲስ ሲሆን ተጠሪነቱ ከአስተዳደር ጉኢው ሆኖ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ተግባራት ያከናውናል።

1. የቤተክርስቲያኑ መንፈሳዊ አስተዳደርና አገልግሎት ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ኃይማኖት እምነትና ሥርዓት ውጭ አለመሆኑን ይቆጣጠራል።

2. ካህናት፤ ዲያቆናት፤ መዘመምራንና ሌሎችም የቤተክርስቲያኑ አገልጋዮች በተመደቡበት ሥራ ላይ በሰዓቱ እየተገኙ ሥራቸውንና መንፈሳዊ አገልግሎታቸውን ሳያጓድሉ ማከናወናቸውን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል።

3. መንፈሳዊ አስተዳዳሪው የካህናት ጉባኤ ሰብሳቢ ይሆናል።

4. እንደአስፈላጊነቱ ከካህናት ጉባኤ ጋር በመመካከር ካህናት ወይም ዲያቆናት እንዲቀጠሩ ከአስተዳደር ጉባኤው ሃሳብ ያቀርባል፤ ስምምነት ላይ ከተደረሰ ካህናትንና ዲያቆናትን በመመዘኛ ይመለምላል፤ በውጤቱ መሠረት ቅጥሩ እንዲፈጸም ከአስተዳደር ቦርዱ ያቀርባል።

5. ሥርዓተ አምልኮን በተመለከተ ካህናት ወይም ዲያቆናት የሥራ ጉድለት ፈጽመው ከተገኘ ሁኔታውን በዝርዝር አጥንቶ ከውሳኔ ሃሳብ ጋር ከአስተዳደር ጉባኤው ያቀርባል።

6. ከካህናት ጉባኤ አባላት ጋር በመመካከርና አስቀድሞ የአስተዳደር ጉባኤውን በማስፈቀድ በበዓላትና በልዩ ልዩ ዝግጅቶች ላይ እንግዶች እንዲገኙ ይጋብዛል። በተመሳሳይ ሁኔታ ከሌሎች ቤተክርስቲያናት ጥሪ ሲመጣም እንዲሁ ከካህናት ጉባኤ ጋር በመመካከር ቤተክርስቲያኑን ወክለው የሚሄዱ አባላትንና መዘምራንን መርጦ ለአስተዳደር ጉባኤው ያሳውቃል።

7. ዘወትር እሁድና በበዓላት ለማህበረ ምዕመናኑ የሚሰጡ የወንጌል ትምህርቶች ሁሉ በርዕሳቸው ላይ ከሚያተኩሩ በስተቀር የምዕመናንን መንፈስ የሚበርዙ የግል ሃሳቦችና አስተያየቶች በትምህርት መልክ እንዳይቀርቡ ይከለክላል።

8. የቤተክርስቲያኑ ማህበረ ምዕመናን ጠቅላላ ስብሰባ፤ የአስተዳደር ጉባኤ ወይም የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ስብሰባዎች ላይ የቤተክርስቲያኑ አስተዳዳሪ ወይም የሚወክለው ካህን እየተገኘ ስብሰባዎችን በጸሎት ይከፍታል ሲጠናቀቁም በጸሎት ይዘጋል።

9. አባላት ቤተክርስቲያኑ የሚሰጣቸውን አገልግሎቶች፤ ማለትም ክርስትና፤ ተክሊል፤ ፍታትና ሌሎችንም በአግባቡ ማግኘታቸውን ይከታተላል። እነዚህ አገልግሎቶች በሕገ ቤተክርስቲያን መሠረት እንዲከናወኑ መፈፀም ያለባቸውን ተግባራትና ዝግጅቶች በጽሑፍ አዘጋጅቶ እንደየሥራቸው ድርሻ ለካህናቱ ጉባኤ አባላትና ለሰንበት

ትምህርት ቤት ክፍል ይሰጣል በግልባጭም አስተዳደር ጉባኤውን ያሳውቃል፡፡

10. በቤተክርስቲያኑ ውስጥ ከሚፈጸሙ የጥምቀትና የጋብቻ ስነስርዓቶች በሚሰጡ የምስክር ወረቀቶች ላይ ይፈርማል፡፡

11. የአስተዳደር ቦርድ አባላት ምርጫ ከመከናወኑ በፊት ምዕመናን ከአገልግሎት እንዲተጉ ይቀሰቅሳል፤ በቂ መንፈሳዊ ግንዛቤ እንዲያገኙ ያስተምራል፡፡

12. የቤተክርስቲያኑ ንዋየ ቅዱሳት መሟላታቸውን ይቆጣጠራል፤ በየጊዜው ቆጠራ እንዲደረግና የጎደለ ካለ እንዲሟላ፤ ያለቀ እንዲተካ፤ ከአገልግሎት የማይውል ካለ ከአስተዳደር ቦርዱ ጋር በመመካከር ለሌሎች ቤተክርስቲያናት በእርዳታ እንዲሰጡ ወይም እንዲሸጡ ያደርጋል፡፡

13. የቤተክርስቲያኑ አባላት ቁጥር በየጊዜው እየጨመረ እንዲሄድ ካህናትንና የአመራር አባላትን በማስተባበር ከመንፈሳዊ ሥራዎች ግንባር ቀደም ሆኖ ቅስቀሳ ያደርጋል፡፡

14. ማህበረ ምዕመናኑን በፍቅርና በአንድነት የሚያስተባብሩ ተግባራትን ያከናውናል፤ ስለዚህም የታመሙትን መጠየቅ፤ የተጣሉትን ማስታረቅ፤ ያዘኑትን ማጽናናት፤ በተለያየ ምክንያት ከቤተክርስቲያን የራቁትንና የተለዩትን ጠይቆ ማቅረብና መመለስ፤ የተቸገሩ እርዳታ የሚያገኙበትን መንገድ መፈለግ፤ በአባላት መካከል ፍጹም የሆነ ፍቅርና አንድነት እንደኖር ማድረግ የመንፈሳዊ አስተዳዳሪ ቀደምት ተግባራት በመሆናቸው በተቻለው መጠን እነዚህን በዕለት ከተዕለት ተግባሩ በማከናወን ለማህበረ ምዕመናኑ አርአያና ምሳሌ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ -21- <u>የኦዲት ኮሚቴ</u> (Audit Committee)

ተጠሪነቱ ለማህበረ ምእመናን ጠቅላላ ጉባኤ ሆኖ የሚከተሉትን ተግባራት የሚያከናውን ሶስት አባላት ያሉት የኦዲት ኮሚቴ በጠቅላላ የማህበረ ምእመናን ጉባኤ ምርጫ ይቋቋማል፤

1- ኮሚቴው ራሱን ችሎ (Independently) የሚሠራ ሲሆን በየ 6 ወር አንድ ጊዜ ለቤተክርስቲያኑ አስተዳደር ጉባኤ፤ በዓመት አንዴ ደግሞ ለምዕመናን አጠቃላይ ጉባኤ የሂሣብ፤ የንብረትና የሥራ እንቅስቃሴ ሪፖርት በጽሁፍ ያቀርባል፡፡ እንዲሁም አጠቃላይ ምርጫ በሚደረግበት ጊዜ ከወጪ ቀሪ ያለውን ሂሳብ መግለጫ በፋይልና በኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎች ተቀርጸው የሚገኙ ማናቸውም ሰነዶችና በቤተክርስቲያኑ ስም የተመዘገቡ ተንቀሳቃሽና የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን በሙሉ መዝግቦ የሚቀጥሉት ተመራጮች በሰነድ እንዲረከቡ ቅድመ ዝግጅቶች ያደርጋል፤ እንደተጠናቀቀም የርክክቡን ሥነ ስርዓት በኃላፊነት ያስፈጽማል፡፡

2- በሂሳብ አያያዝ፤ በሪፖርት አቀራረብ፤ በንብረት አጠባበቅና በማናቸውም ደረጃ በቤተክርስቲያኑ የሥራ እንቅስቃሴ ወይም አፈጻጸም ላይ ጉድለት ቢያገኝ ጉድለት ያደረሰውን ሰው መተማመኛ ካስፈረመ በኋላ ከጠቅላላ የምዕመናን ጉባኤ ውሳኔ በማቅረብ በፌደራልና በፔንስልቫኒያ ሕጎች መሠረት ተጠያቂነት እንዲኖረው ያደርጋል።

3- ኮሚቴው የሂሳብ ሰነዶችና መዛግብትን በማናቸውም ጊዜ የማየትና ጠይቆ የመረዳት መብትና ሥልጣን እንዳለው በየትኛውም ደረጃ የሚገኙ የቤተክርስቲያኑ ተመራጮች አውቀው አስፈላጊውን የሥራ ትብብር ያደርጉለታል።

4- ኮሚቴው የቤተክርስቲያኑ ሂሣብ፤ ልዩ ልዩ ሰነዶችና ተንቀሳቃሽ ንብረቶች አስተማማኝ በሆነ መንገድ እንዲያዙ ከሚመለከታቸው ክፍሎች ይጠቁማል፤ ዘደዎችን እየቀየሰ ይሰጣል። በተጨማሪም የሥራ ልምዶችን ከማሻሻል ከውጭ ባለሙያዎች የሚሠነዘሩ ሃሳቦችና አስተያየቶችን (recommendations) ተግባራዊ ያደርጋል።

5- ኮሚቴው የሂሳብ ሰነዶችን መርምሮ ከማረጋገጥ ከውጭ ተቀጥረው ከሚሠሩ ባለሞያዎች (Certified Public Accountants) ጋራ ይተባበራል።

6- ኮሚቴው አንድ ሰብሳቢና አንድ ጸሐፊ የሚኖረው ሲሆን፤ የራሱን የሥራ መመሪያ አዘጋጅቶ ይሠራል።

7- የኮሚቴው አባላት የአገልግሎት ዘመን ከሶስት ዓመት ሆኖ የአገልግሎት ዘመናቸውን የፈጸሙ አባላት እንደገና ለሌላ የአገልግሎት ዘመን ከመመረጥ ይችላሉ።

አንቀጽ -22- <u>የአማካሪዎች ጉባኤ</u>

ሀ- በካህናት፤ በአመራር አባላትና በምዕመናን መካከል በሥራ ምክንያት አለመግባባት ቢፈጠር ጉዳዩን ተመልክቶ የመፍትሄ ሃሳብ የሚያቀርብ፤ በሚያቀርበው የመፍትሄ ሃሳብ ስምምነት ካልተደረሰ ጉዳዩን ከውሳኔ ሃሳብ ጋር ከማህበረ ምዕመናን ጠቅላላ ጉባኤ አቅርቦ የሚያስወስን አምስት አባላት ያሉት የአማካሪዎች ጉባኤ ይቋቋማል።

ለ- የማህበረ ምዕመናን ጠቅላላ ጉባኤ የአማካሪዎች ጉባኤ አባላትን መርጦ ይሰይማል።

ሐ- የኮሚቴው የአገልግሎት ዘመን ለአምስት ዓመታት ይሆናል፤ ሆኖም አባላት ለሌላ የአገልግሎት ዘመን እንዲያገለግሉ በጉባኤው ሊጠየቁ ይችላሉ።

መ- ጉባኤው የራሱን ሊቀመንበርና ፀሐፊ መረጦ ሥራውን ያከናውናል።

አንቀጽ -23- <u>የአስተዳደር ጉባኤው ለቤተክርስቲያኑ እድገትና የአገልግሎት መጠናከር ይጠቅማሉ ብሎ የሚያምንባቸውን፤ እንደ መንፈሳዊ ትምህርት ክፍል፤ የእቅድና ልማት ክፍል፤ የሕንጻ ጥገናና እድሳት ክፍል የመሳሰሉ የሥራ ክፍሎችን ያቋቁማል፤ የሥራ ኃላፊነታቸውንም ይወስናል።</u>

አንቀጽ -24- <u>የሰንበት ትምህርት ቤት ክፍል፥</u>

የሰንበት ትምህርት ቤት ክፍል ተጠሪነቱ ለአስተዳደር ጉባኤ ሆኖ መንፈሳዊ ጉዳይን በተመለከተ ግንኙነቱን ከካህናት ጉባኤ ጋር በማድረግ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል፦

1- በሰንበትና በሌሎች ዓበይት በዓላት የዕለትና የዘወትር መርሐ ግብር በማውጣት የቤተክርስቲያን ሕግና ሥርዓት፤ የኃይማኖት ትምህርት፤ የቅዳሴ ተሰጥዎና የቅዱሳት መጽሐፍት ጥናት እንዲሰጥ ያደርጋል።

2- ለምዕመናን ትምህርት የሚሰጡ መንፈሳዊ መዝሙራትን ያቀርባል።

3- ሕፃናትና ወጣቶች ከኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት እምነት እንዳይወጡ የቤተክርስቲያንን ሕግና ሥርዓት እንዲያውቁና እንዲያከብሩ፤ ከአስተዳደር ጉባኤ ጋር በመተባበር በቅርብ እየተከታተለ ያስተምራል፤ ይመክራል፤ ይቆጣጠራል። እንዲሁም እንደየ እድሜያቸው ክልል በመከፋፈል መንፈሳዊ መዝሙሮችን እንዲያጠኑና እንዲዘምሩ ያደርጋል።

4- ወጣቶች መንፈሳዊ ዕውቀታቸውን እንዲያዳብሩ ሥዕሎችና ልዩ ልዩ የመማሪያ መሣሪያዎች ተሟልተው እንዲገኙ ጥረት ያደርጋል።

5- የሰንበት ትምህርት ቤት ተማሪዎች በበዓላትም ሆነ በአጋጣሚ ጊዜ በትያትር መልክ መንፈሳዊ ዝግጅት ለማቅረብ ሲዘጋጁ ይህንኑ ለአስተዳደር ጉባኤውና ለክህናት ጉባኤ በማቅረብ እንደተፈቀደ በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል።

6- የሰንበት ትምህርት ቤት ተማሪዎች በትያትር ዝግጅት፤ በመንፈሳዊ ካሴቶችና በዓማናዊ ሥዕሎች ሽያጭም ሆነ በማናቸውም ሁኔታ የሚሰበስቡት ገንዘብ ለቤተክርስቲኑ ገቢ ይሆናል። ለሰንበት ትምህርት ክፍል የሚያስፈልገውን በጀት በማዘጋጀት ለአስተዳደር ጉባኤው በማቅረብ ያስፈቅዳል።

7- በሰንበት ትምህርት ቤት ክፍልና በካህናት ጉባኤ መካከል የአሰራር ችግር ቢፈጠር ጉዳዩ ለአስተዳደር ጉባኤ ቀርቦ ውሳኔ እንዲያገኝ ይደረጋል።

አንቀጽ -25- <u>መተዳደሪያ ደንቡን ስለማሻሻልና ስለማጽደቅ</u>

25.1 <u>ማሻሻል፦</u>

25.1.1 አስፈላጊነቱ ከታመነበትና በአባል ምዕመናን ደረጃ ውይይት ተደርጎበት እንዲሻሻል የአባላቱን 2/3ኛ ድምጽ ካገኘ፤ ይህ መተዳደሪያ ደንብ በማናቸውም ጊዜ ሊሻሻል ይችላል።

25.1.2 ደንቡ እንዲሻሻል የአባላቱን የድጋፍ ድምጽ ለማግኘት በሚጠራ አጠቃላይ የምዕመናን ስብሰባ ምልዓተ ጉባኤ የሚኖረው ከተመዘገቡና የአባልነት ክፍያቸውን አጠናቀው ከከፈሉ አባላት ቁጥር ሁለት ሦስተኛው (2/3ኛ) የተገኙ እንደሆነ ብቻ ነው።

25.1.3 ከአስተዳደራዊ መዋቅር በስተቀር ደንቡ ሲሻሻልና ሲቀየር በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተክርስቲያናት የሚመሩበትን ቃለ አዋዲ መሠረት በማድረግ ይሆናል።

25.1.4 ደንቡን ማሻሻል አስፈላጊነቱ ታምኖበት በአባል ምዕመናን ድምፅ ከጸደቀ ከቤተክርስቲያኑ አባላት መካከል የደንብ አሻሻይ ኮሚቴ በምዕመናን ጉባኤ ይመረጣል፤ የሚመረጠውም ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለምዕመናን ጉባኤ ይሆናል።

25.2 <u>ማጽደቅ</u>

25.2.1 ይህ ደንብ በምዕመናን ጉባኤ ከጸደቀ በኋላ በወቅቱ በሥራ ላይ በሚገኙት የቤተክርስቲያኑ የአስተዳደር ጉባኤ አባላት ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

25.2.2 ይህ ደንብ August 18 ቀን 2012 ዓም በፊላደልፊያ ከተማ ተፈረመ።